8L0 0D0250/5
9/01/2011

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Urban Development & Housing

752/2013

ለከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ
<u>ከ/ል/ቤ/ሚ</u>

ጉዳዩ፡ <u>የጸደቀ መመሪያ ስለመላክ</u>

የልማት ኃይሎች የዕውቅናና የሽልማት መመሪያ ቁጥር 64/2011 ሆኖ ከመስከረም 8 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንዲሆን የጸደቀ በመሆኑ የመመሪያውን ተፈጻሚነት እንድትከታተሉና እንድታስፈጽሙ የጸደቀውን 1 ጥራዝ መመሪያ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ጃንጥራር አባይ ይግዛው
ሚኒስትር

ግልባጭ፡-

- ለክብርት ሚኒስትር ዴኤታ ( የከተማ ልማት ዘርፍ)፣
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ ( የቤቶችና መሠረተ ልማት ዘርፍ)፣
- ለሚኒስትር ጽ/ቤትና ሚኒ ካቢኔጉዳዮች ቢሮ
- ለሕግ ዳይሬክቶሬት

<u>ከ/ል/ቤ/ሚ</u>

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT & HOUSING

የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም
Ethiopian Urban Forum

# የልማት ኃይሎች የዕውቅናና የሽልማት

# መመሪያ ቁጥር 752/2013

መስከረም 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# መግቢያ

በአገራችን በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ እየፈጠረ ያለው የሥራ ዕድል በቀላል የማይገመት ሲሆን ከጊዜ ወደ ጊዜም በከፍተኛ ደረጃ እያደገ የመጣ ሲሆን የኢንተርፕራይዞች ልማት ለኢዱስትሪውም ዕድገት ሰፊ መሠረት እየጣለ በመምጣት ላይ የሚገኝ በመሆኑ፣

በየደረጃው የሚገኙትን ሞዴል ኢንተርፕራይዞች መካከል ከየዘርፉ የላቀ አፈጻጸም ያላቸውን በመለየት እንዲሁም በየክልሉ ወደ ታዳጊ መካከለኛ ባለሀብትነት የተሸጋገሩትን ኢንተርፕራይዞች በመለየት ዕውቅናና ሽልማት በመስጠት እርስ በርስ እንዲማማሩና በመካከላቸው ጤናማ የውድድር መንፈስ በመፍጠር የዘርፉን ዕድገት ማጎልበት አስፈላጊ በመሆኑ፣

እንዲሁም ከስደት ተመላሽ በሆኑ ዜጎች የተቋቋሙ ኢንተርፕራይዞች እና የሴት ኢንተርፕርነር ልማት ፕሮጀክት/WEDP/ ተጠቃሚ በመሆን ውጤታማ የሆኑ በሴቶች የተቋቋሙ ኢንተርፕራይዞችን በመለየት ዕውቅናና እና ሽልማት መስጠት እንዲሁም በዘርፉ የፈጠራ ሥራ ያላቸው ወጣቶች እና ሴቶችን ማበረታታት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

እንዲሁም ሌሎች የልማት ኃይሎች ማለትም በየክልሎች እና በየከተሞቹ የሚገኙ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ተቋማት፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት፣ የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት በመለየት ዕውቅናና እና ሽልማት በመስጠት ማበረታታት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ዕውቅና እና ሽልማት የሚሰጣቸውን የልማት ኃይሎች ለመምረጥ የሚረዳ መመዘኛ መስፈርት፣ የውድድሩን ሂደት ግልጽ ለማድረግ እና የዕውቅናና ሽልማት ዓይነት ለመወሰን መመሪያ ማዘጋጀት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 916 አንቀጽ 26 ሥር ተዘርዝረውየተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት ለመተግበር ያመቻቸው ዘንድ ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የልማት ኃይሎች የዕውቅና እና የሽልማት መመሪያ ቁጥር 752/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓም

1) "ኢንተርፕራይዝ" ማለት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሆነው ከአነስተኛ አምራች ዘርፍ ውጭ በስትራቴጂው መሠረት የተደራጁ ተቋማት ማለት ነው፡፡

2) "የከተሞች ፎረም" ማለት በከተማ ልማትና ቤቶች ዘርፍ አጀንዳዎች ዙሪያ ጠንካራ መሰረት ያሰዉ የከተማ ህዝብ ንቅናቄና ተጠቃሚነት ለመፍጠር እንዲቻል በየሁለት ዓመቱ የሚከበር የኢትዮጵያ ከተሞች በአል ማለት ነው፡፡

3) "የልማት ኃይሎች" ማለት በየክልሉች እና በየከተሞቹ የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች እና ለኢንተርፕራይዞች እድገት የላቀ ድጋፍ የሰጡት ተቋማት ማትት ነው፡፡

4) "ዕውቅና" ማለት በዚህ መመሪያ በተቀመጡ መስፈርቶች መሠረት ለተለዩ ኢንተርፕራይዞች እና ተቋማት በኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የሚሰጥ ሠርተፍኬት ወይም ማንኛውም አይነት ማበረታቻ ማለት ነው፡፡

5) "ሽልማት" ማለት በዚህ መመሪያ በተቀመጡ መስፈርቶች መሠረት ለተለዩ ኢንተርፕራይዞች እና ተቋማት በኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ለማበረታቻነት የሚሰጥ በገንዘብ ወይም ማንኛውም በዓይነት የሚሰጥ ዕቃ ማለት ነው፡፡

6) "ሞዴል ኢንተርፕራይዝ" ማለት በዚህ መመሪያ በተቀመጡ መስፈርቶችን በማሟላት የሚመረጡ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ማለት ነው፡፡

7) "ደጋፊ ተቋም" ማለት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት እድገት እራሳጊውን ድጋፍ ያደረጉ ተቋማት ማት ነው፡፡

8) ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

* የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር * አነስተኛ ማስፋፊያ ኤጀንሲ

3. የመመሪያው ዓላማ

1) ዋና ዓላማ

በዘርፉ ከሚገኙ የልማት ኃይሎች ውስጥ ውጤታማ የሆኑ ኢንተርፕራይዞችን፣ ደጋፊ ተቋማትን እና ሌሎች ለዘርፉ አስተዋጽኦ ያበረከቱ አካላትን ለይቶ እውቅናና ሽልማት በመስጠት በሌሎች ላይ ጤናማ የውድድር መንፈስ በማሳደር በዘርፉ የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ ለማጎልበት ነው፡፡

2) ዝርዝር ዓላማዎች

ሀ) በየክልሉ በሞዴልነት ከተመረጡ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች (ከአነስተኛ አምራች/ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጭ) መካከል ከእያንዳንዱ ዋና ዋና ንዑስ ዘርፍ ከ1-3 የወጡትን ሞዴል ኢንተርፕራይዞች እና በየበጀት አመቱ ከጥቃቅንና አነስተኛ ወደ ታዳጊ መካከለኛ የተሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች ዕውቅናና ሽልማት በመስጠት ጤናማ የውድድር መንፈስ ለመፍጠር፣

ለ) በየክልሎች እና በየከተሞቹ የሚገኙ በሴቶች፣ ከስደት ተመላሽ በሆኑ ዜጎች፣ በተመራቂዎች፣ በአካል ጉዳተኛ የተቋቋሙ ኢንተርፕራይዞች፣ በዘርፉ ፈጠራ ያላቸውን ወጣቶች እንዲሁም የWEDP ፕሮግራም ተጠቃሚ በመሆን ውጤታማ የሆኑ በሴቶች የተቋቋሙ ኢንተርፕራይዞችን በመለየት ዕውቅናና ሽልማት በመስጠት ጤናማ የውድድር መንፈስ ለመፍጠር፣

ሐ) በዘርፉ የፈጠራ ሥራ ያላቸው ወጣቶች እና ሴቶችን በማበረታታት ዘርፉ የፈጠራ ሥራዎች እንዲያድጉ ለማድረግ፣ እና

መ) በየክልሎች እና በየከተሞቹ የሚገኙ ለኢንተርፕራይዞች የላቀ ድጋፍ የሰጡትን የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ተቋማት፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት፣ የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት በመለየት ዕውቅናና ሽልማት በመስጠት ጤናማ የውድድር መንፈስ ለመፍጠር ነው፡፡

4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ የልማት ኃይሎች የዕውቅናና የሽልማት መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆነው፡-

1) በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ደረጃ (ከአነስተኛ አምራች ዘርፍ ውጭ) መስፈርቱን አሟልተው በሞዴልነት የተመረጡ ኢንተርፕራይዞች፣
2) በዩኒቨርሲቲና በቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ምሩቃን የተቋቋሙ እና ውጤታማ የሆኑ ኢንተርፕራይዞች፣
3) አዳዲስ የፈጠራ ሥራ ያላቸው ኢንተርፕራይዞች እና በዘርፉ የፈጠራ ሥራ ያላቸው ወጣቶች፣

4) በሴቶች፣ ክስደት ተመላሽ በሆኑ ዜጎች እና በአካል ጉዳተኛ የተቋቋሙ እና ውጤታማ የሆኑ ኢንተርፕራይዞች፣

5) በWEDP ፕሮጀክት ውጤታማ የሆኑ ሴት ኢንተርፕርነሮች፣

6) በየበጀት ዓመት ወደ ታዳጊ መካከለኛ የተሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች፣

7) ለኢንተርፕራይዞች የላቀ ድጋፍ የሰጡት የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ተቋማት፣

8) ለኢንተርፕራይዞች የላቀ ድጋፍ የሰጡት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት፣

9) ለኢንተርፕራይዞች የላቀ ድጋፍ የሰጡት የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት፣ እና

10) በዘርፉ የተሻለ አፈጻጸም ያስመዘገቡ የከተማ ልማትና ቤቶች ዘርፍ ተቋማት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ኢንተርፕራይዝ የልማት ኃይሎች መመልመያ መስፈርቶችና የውድድር አካሄድ

5. የኢንተርፕራይዞች የቅድመ-ማወዳደሪያ መስፈርቶች እና ለውድድሩ መቅረብ ያለባቸው ማስረጃዎች

1) የኢንተርፕራይዙ የንግድ ፍቃድ/የማህበር ምሥክር ወረቀት የታደሰና የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ያለው፣
2) ለኢንተርፕራይዙ ቅጥር ሰራተኞች እና ለአባላት ክፍያ የተደረገበት የክፍያ ሰነድ፣
3) የተሟላ የሂሳብ መዝገብና ሰነድ እና የተረጋገጠ የኦዲት ሪፖርት፣
4) በመስፈርቱ የቀረቡ ነጥቦች ላይ የሚያወዳድራቸው ጉዳዮችን በኤግዚቢትነት ይዞ መገኘት /በፎቶ ወይንም በቪዲዮ ይዞ መቅረብ /የሚችል፣
5) ከሞዴል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች (ከአነስተኛ አምራች ዘርፍ ውጭ) መካከል በዕውቅናና ሽልማት ፕሮግራሙ ላይ መሳተፍ የሚችሉት በዚህ መመሪያ በተቀመጡት መስፈርቶች ተመዝነው አጠቃላይ ከየንዑስ ዘርፉ ከ1-3 የወጡ ኢንተርፕራይዞች እና በበጀት አመቱ ወደ ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዝነት የተሸጋገሩ፣
6) የሞዴል ኢንተርፕራይዝ የመወዳደሪያ ነጥባቸው 75% እና ከዚያ በላይ ያላቸው፣
7) በልማት ሠራዊት አደረጃጀት እና አሰራር መሰረት የሚንቀሳቀሱ፣
8) በሴት የተቋቋሙ ኢንተርፕራይዞች ከማወዳደሪያ ነጥባቸው ቢያንስ 65% ውጤት ያስመዘገቡ፣
9) በምሩቃን የተቋቋሙ ኢንተርፕራይዞች ከማወዳደሪያ ነጥባቸው ቢያንስ 55% ውጤት ያስመዘገቡ፣
10) በፈጠራ ሥራቸው ዕውቅና የሚሰጣቸው ኢንተርፕራይዞች ከማወዳደሪያ ነጥባቸው ቢያንስ 50% ውጤት ያስመዘገቡ፣ እና
11) በአካል ጉዳተኞች የተቋቋሙ ኢንተርፕራይዞች ከማወዳደሪያ ነጥብ ቢያንስ 50% ውጤት ያስመዘገቡ ሲሆኑ ይገባቸዋል።

6. የሞዴል ኢንተርፕራይዞች የሥራ መስክ እና መመልመያ መስፈርቶች

በኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ዕውቅናና ሽልማት ላይ ለመሳተፍ የሚመረጡት ኢንተርፕራይዞች፡-

1) ሞዴል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሁሉም ከዕድገት ተኮር ዘርፎች የማኑፋክቸሪንግ፣ ኮንስትራክሽን፣ ከተማ ግብርና፣ ማዘጋጃቤታዊና ሌሎች አገልግሎቶች ሥራዎች ይሆናሉ።

2) በንዑስ ዘርፎች ከጨርቃ-ጨርቅና አልባሳት፣ ከቆዳና ቆዳ ውጤቶች፣ ከእንጨት፣ ብረታ-ብረትና ኢንጂነሪንግ፣ ዕደ ጥበብና ጌጣጌጥ፣ ከማዕድንና ኬሚካል ምርት ሥራዎች፣ ከአግሮ-ፕሮሰሲንግ፣ ከግንባታ ግብአት ምርቶች፣ ከሥራ-ተቋራጭነት፣ ከኮብልስቶን፣ ከመሰረተ ልማት ግንባታ፣ ከማዕድን ሥራዎች፣ ከከተማ ግብርና፣ ከማዘጋጃቤታዊና ሌሎች አገልግሎቶች ላይ የተሰማሩ ሲሆኑ እንደ ሥራ ባህርያቸው የጋራና የተናጠል የመምረጫ መስፈርቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

3) በማንኛውም ዘርፍ የተለየ የፈጠራ ሥራ ያላቸው ጥቃቅንና አነስተኛ ሞዴል ኢንተርፕራይዞች ተወዳድረው ሊሳተፉ ይችላሉ።

4) በዚህም መሰረት ከሞዴል መምረጫ መስፈርቶች በተጨማሪ የሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦች በማወዳደሪያነት ግንዛቤ ውስጥ ሊገቡ ይገባል።

ሀ) በጨርቃ-ጨርቅና አልባሳት ንዑስ ዘርፍ (በሽመና ውጤቶች፣ በሹራብ ሥራ፣ በልብስ ስፌትና በጥልፍ ሥራ) ለተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች

(1) ለሚያመርቷቸው ምርቶች የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃን የሚጠቀም መሆኑ፣

(2) የሚያመርቷቸው ምርቶች ከውጭ የሚገቡትን የሚተኩ መሆናቸው፣

(3) ከተገልጋይ እይታ አንጻር የምርቶቹ ዲዛይንና ማራኪነት፣

(4) የሚፈለገውን ያህል ምርት በብዛት ለማምረት የሚያስችል የተለየ አሰራር ዘዴ ያለው መሆኑ፣

(5) የጠባቂነትና የጥገኝነት አመለካከትና ዝንባሌ የሌለው መሆኑ፣

(6) በኢንተርፕራይዙ ውስጥ የሚገኙ ባለሙያዎች የሙያ ብቃት ምዘና ያለፉ መሆናቸው፣

(7) ለውጭ ሀገር ገበያ ሊቀርብ የሚችል ጥራት ያለው ምርት እያቀረበ የሚገኝ/ ማቅረብ የሚችል መሆኑ፣ እና

(8) የካይዘን ስራ አመራር ፍልስፍናን ተግባራዊ እያደረገ መሆኑ የተረጋገጠ ናቸው።

ለ) በቆዳና ቆዳ ውጤቶች ሥራ የተሰማሩ

(1) ለሚያመርቷቸው ምርቶች የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃን የሚጠቀም መሆኑ፣

(2) ለሚያመርቷቸው ምርቶች ከውጭ የሚገቡትን የሚተኩ መሆናቸው፣

(3) ከተገልጋይ እይታ አንጻር የምርቶቹ ዲዛይንና ማራኪነት፣

(4) የሚፈለገውን ያህል ምርት በብዛት ለማምረት የሚያስችል የተለየ አሰራር ዘዴ ያለው መሆኑ፣

(5) የጠባቂነትና የጥገኝነት አመለካከትና ዝንባሌ የሌለው መሆኑ፣

(6) በኢንተርፕራይዙ ውስጥ የሚገኙ ባለሙያዎች የሙያ ብቃት ምዘና ያለፉ መሆናቸው፣

(7) ለውጭ ሀገር ገበያ ሊቀርብ የሚችል ጥራት ያለው ምርት እያቀረበ የሚገኝ ማቅረብ የሚችል መሆኑ፣

(8) በአመራረት ሂደቱ የአካባቢን ብክለት ለመቀነስ/ለማስወገድ ያደረገው ጥረት በማስረጃ

ታሳቢ፣ የሚደረጉ ጉዳዮች ናቸው፣

(9) የተለያዩ የምርት አይነት አማራጮችን ማምረት የሚችል፣

(10) የካይዘን ስራ አመራር ፍልስፍናን ተግባራዊ እያደረገ መሆኑ የተረጋገጠ፣

ሐ) የእንጨት፣ ብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ሥራ መስክ የተሰማሩ

በዚህ ዘርፍ የሚጠቃለሉት ዋና ዋና የሥራ መስኮች የእንጨትና የቀርቀሃ ውጤቶችና የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ናቸው።

(1) በራሳቸው ወይም በሌላ ኢንተርፕራይዝ በአገር ውስጥ በተሰራ የማምረቻና መገልገያ መሳሪያ መጠቀማቸው፣

(2) የሚያመርቷቸው ምርቶች ከውጭ የሚገቡትን የሚተኩ መሆናቸው፣

(3) የሚፈለገውን ያህል ምርት በብዛት ለማምረት የሚያስችል የተለየ አሰራር ዘዴ ያለው መሆኑ፣

(4) በኢንተርፕራይዙ ውስጥ የሚገኙ ባለሙያዎች የሙያ ብቃት ምዘና ያለፉ ስለመሆናቸው፣

(5) የጠባቂነትና የጥገኝነት አመለካከትና ዝንባሌ የሌለው መሆኑ፣

(6) የተለያዩ የምርት አይነት አማራጮችን ማምረት የሚችል፣

(7) የካይዘን ስራ አመራር ፍልስፍናን ተግባራዊ እያደረገ መሆኑ የተረጋገጠ።

መ) በማዕድንና ኬሚካል ሥራዎች የተሰማሩ

በማዕድን የስራ መስክና በኬሚካል የስራ ዘርፍ ለሚወዳደሩ አንተርፕራይዞች ከሞዴል ኢንተርፕራይዞች መምረጫ መስፈርት በተጨማሪ የሚከተሉት ነጥቦች ሊታዩ ይገባል።

(1) በራሳቸው ወይም በሌላ ኢንተርፕራይዝ በአገር ውስጥ በተሰራ የማምረቻና መገልገያ መሣሪያ መጠቀማቸው፣

(2) ከውጭ ሀገር የሚገቡ ምርቶችን ለመተካት መቻላቸው፣

(3) ኢንተርፕራይዙ የምርት ጥራትና ብዛትን ለማሻሻል የተለየ የአሰራር ዘዴ ያለው መሆኑ፣

(4) የካይዘን ስራ አመራር ፍልስፍናን ተግባራዊ እያደረገ መሆኑ የተረጋገጠ፣

(5) የምርት አስተሻሸግ፣ የጥራት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ያላቸው መሆኑ፣

(6) በአመራረት ሂደቱ የአካባቢን ብክለት ለመቀነስ/ለማስወገድ ያደረገው ጥረትና በተለይም ምርቶቹ ለጤንነት የማያሰጉ መሆናቸው በዋነኝነት ታሳቢ የሚደረጉ ጉዳዮች ናቸው።

ሠ) በዕደ-ጥበብ ውጤቶች የተሰማሩ

በዚህ የሥራ ዘርፍ ለሚወዳደሩ ኢንተርፕራይዞች ከሞዴል ኢንተርፕራይዞች መምረጫ መስፈርት በተጨማሪ የሚከተሉት ነጥቦች ሊታዩ ይገባል።

(1) በራሳቸው ወይም በሌላ ኢንተርፕራይዝ በአገር ውስጥ በተሰራ የማምረቻና መገልገያ መሣሪያ መጠቀማቸው፣

(2) ኢንተርፕራይዙ የምርት ጥራትና ብዛት ለማሻሻል የተለየ የአሰራር ዘዴ ያለው መሆኑ

(3) የአካባቢ ባህላዊ እሴቶችን የሚያንጸባርቁ

(4) ከፍተኛ የቱሪስት መስህብነት ደረጃ ያላቸው

(5) የካይዘን ስራ አመራር ፍልስፍናን ተግባራዊ እያደረገ መሆኑ የተረጋገጠ።

ረ) በአግሮ-ፕሮሰሲንግ እና ምግብ ማቀነባበር የተሰማሩ

(1) የኢንተርፕራይዙ ምርት የቆይታ ጊዜና ጣዕም ያስመቀየር ባህርይ፣

(2) ከውጭ የሚገቡ የደረቁ ምግቦችን ለመተካት ያደረገው ጥረትና ያስመዘገበው ውጤት፣

(3) ኢንተርፕራይዙ የምርት ጥራትና ብዛትን ለማሻሻል የተለየ የአሰራር ዘዴ ያለው መሆኑ፣

(4) ምርቶቹ ለውጭ ሀገር ገበያ ቀርበው ተፈላጊ መሆናቸው/ለያቀርቡ የሚችሉ መሆናቸው፣

(5) የምርት አስተሻሸግና፣ የጥራት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ያላቸው መሆኑ

(6) በአመራረት ሂደቱ የአካባቢን ብክለት ለመቀነስ/ለማስወገድ ያደረገው ጥረትና በተለይም ምርቶቹ ለጤንነት የማያሰጉ መሆናቸው በዋነኝነት ታሳቢ የሚደረጉ ጉዳዮች ናቸው።

(7) የካይዘን ስራ አመራር ፍልስፍናን ተግባራዊ እያደረገ መሆኑ የተረጋገጠ።

ሰ) በኮንስትራክሽን የሥራ ዘርፍ የተሰማሩ

በዚህ ዘርፍ የሚጠቃለሉት በግንባታ ግብዓት አቅራቢነት (ፕሪካስት፣ ብሎኬት፣ ጥርብ የኮብል ስቶን ማቅረብ፣ አግሮ ስቶን፣ ጅብሰም ቦርድ፣ ጠጠር፣) እና የግንባታ አገልግሎት ስራዎች፣ የግንባታ ሥራ፣ የማጠናቀቂያ ሥራዎች፣ የመንገድ ስራ፣ የኤሌክትሪክ ዝርጋታ፣ የቧንቧ ስራ እና የሳኒቴሽን ስራዎች የተሰማሩትን ያጠቃልላል።

(1) በራሳቸው ወይም በሌላ ኢንተርፕራይዝ በአገር ውስጥ በተሰራ የማምረቻና መገልገያ መሣሪያ መጠቀማቸው፣

(2) ለየሚፈለገውን ያህል ምርት በብዛትና በጥራት ለማምረት የሚያስችል የተለየ አሰራር ዘዴ ያለው መሆኑ፣

(3) በኢንተርፕራይዙ ውስጥ የሚገኙ ባለሙያዎች የሙያ ብቃት ምዘና ያለፉ መሆናቸው፣

(4) የጠባቂነትና የጥገኝነት አመለካከትና ዝንባሌ የሌለው መሆኑ፣

(5) ለኮንስትራክሽን አገልግሎት የሚውል ለየት ያለ የሀገር ውስጥ ጥሬ-ዕቃ ጥቅም ላይ ማዋሉ፣

(6) በኮንስትራክሽን ሥራ ላይ የመልካም ሥራ ማረጋገጫ ያለው መሆኑ በዋነኛነት የሚዳሰሱ ጉዳዮች ናቸው።

(7) የካይዘን ስራ አመራር ፍልስፍናን ተግባራዊ እያደረገ መሆኑ የተረጋገጠ።

### ሸ) በከተማ ግብርና የተሰማሩ

በዚህ ዘርፍ የሚጠቃለሉት በከተማ እርሻ ማለትም በአትክልት፣ ፍራፍሬ፣ የእህል ምርት፣ ችግኝና የመሳሰሉት እና በእንስሳት እርባታና ማድለብ ንዑስ ዘርፍ በግ፣ ፍየል፣ ዶሮ፣ ንብ፣ ከብት፣ አሳማ በመሳሰሉት የሥራ መስኮች የተሰማሩ ናቸው።

(1) የሚጠቀምበት የመሬት ይዞታ ስፋት/በአነስተኛ ቦታ ብዙ ማምረት መቻል/፣

(2) እንደ ምርቱ ዓይነት /በቀን፣ በሳምንት፣ በወር/ ለገበያ የሚያቀርበው የምርት መጠን፣

(3) በዘመናዊ መንገድ የማቀነባበር ወይም የምርቱን የቆይታ ጊዜ ለማራዘም ያደረገው ጥረት በዝርዝር ሲታዩ የሚገባቸው ጉዳዮች

(4) የካይዘን ስራ አመራር ፍልስፍናን ተግባራዊ እያደረገ መሆኑ የተረጋገጠ።

### ቀ) በማዘጋጃቤታዊና ሌሎች አገልግሎቶች የተሰማሩ

በከተሞች ጎልቶ የሚታየውን የድህነትና ሥራ አጥነት ችግር ለመቀነስ አዋጭ ተብለው ከተለዩትና ከፍተኛ ትኩረት ከተሰጣቸው የሥራ ዘርፎች መካከል የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ሥራዎች ይጠቀሳሉ። በዚህ ንዑስ ዘርፍ የሚካተቱት የሥራ መስኮች ደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብና ማጓጓዝ፣ የአካባቢ /መንገድ/ ጽዳት፣ የሕዝብ ንጽህና ቤቶች አገልግሎት፣ የከተማ ማስዋብ ሥራ እና የዘላቂ ማረፊያ ቤት ማዘጋጀትና አካባቢውን ማስዋብ ሥራዎች ይገኙበታል።

በዚህ የሥራ ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ እንደሌሎች ኢንተርፕራይዞች ለመወዳደር ከሞዴል ኢንተርፕራይዞች መምረጫ መስፈርት በተጨማሪ የሚከተሉት ነጥቦች ሲታዩ ይገባል።

(1) ደረጃውን በጠበቀ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ላይ ደረቅ ቆሻሻዎችን የማስወገድ ሁኔታ፣

(2) የተሰበሰቡ ቆሻሻዎችን በመልሶ ዑደት በመጠቀም ለአገልግሎት የማዋል ደረጃ፣ እና

(3) ኢንተርፕራይዙ በከተማው ውስጥ ያስዋባቸው አካባቢዎች ብዛት ናቸው።

## 6. በዩኒቨርስቲ እና በቴክኒክና ሙያ ምሩቃን የተቋቋሙ ኢንተርፕራይዞችን ዕውቅናና ሽልማት ለመስጠት የተዘጋጀ መስፈርት

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት የሥራ ዕድል መፍጠሪያ ከመሆን ባሻገር ለኢንዱስትሪው ልማት መሰረት የሚሆኑ ልማታዊ ባለሀብቶች የሚፈጠሩበት ዘርፍ መሆኑ በስትራቴጂው ተመላክቷል። በዚህ አግባብ የዘርፉ ልማት አፈፃፀም እንደሚያመላክተውም በርካታ የዩኒቨርስቲ እና የኮሌጅ ምሩቃን ምሩቃን ለራሳቸው የሥራ ዕድል ከመፍጠር አልፈው ለበርካታ ወጣቶችና ሴቶች ሥራ በመፍጠርና በማኑፋክቸሪንግ እና በሌሎች ዘርፎች በማሳተፍ ለኢንዱስትሪው ልማት ሽግግር መሠረት በመጣል ላይ ይገኛሉ።

ስለሆነም ለእነዚህ ወጣት ምሩቃን እውቅናና ሽልማት በመስጠት ማበረታታት ለዘርፉ ልማት ስትራቴጂ ስኬታማነት የሚኖረውን ጠቀሜታ ከግምት ውስጥ በማስገባት በፌዴራል ደረጃ በሚዘጋጀው የዕውቅናና የሽልማት ፕሮግራም ላይ እውቅናና ሽልማት የሚሰጣቸውና የሚሸለሙትን ለመለየት የሚከተለው መስፈርት ተዘጋጅቷል፡፡

ሠንጠረዥ 1፡ የዩኒቨርስቲና የኮሌጅ ምሩቃንን ማወዳደሪያ መስፈርት

| ተ.ቁ | የመስፈርቱ ዓይነት | ኢንተርፕራይዙ የተቋቋመበት ዘመን | የተሰጠው ነጥብ% | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ከዩኒቨርስቲ የተመረቀ/ች እና የራሱን/ሷን ኢንተርፕራይዝ ያቋቋመች | 2006 | 10 | 15 |
| | | 2007 | 12 | |
| | | 2008 | 13 | |
| | | 2009 | 15 | |
| 2 | የተሰማራበት የሥራ ዘርፍ | በማኑፋክቸሪንግ፣ በኬሚካል ኢንዱስትሪ እና በከተማ ግብርና ዘርፍ የተሰማራ/ች | 15 | 15 |
| | | በኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሰማራ/ች | 10 | |
| | | በማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት የተሰማራ/ች | 8 | |
| 3 | የሥራ ዕድል የፈጠረው/ችው | ከ3 - 5 | 10 | 20 |
| | | ከ6 - 10 | 15 | |
| | | ከ11 - 15 | 18 | |
| | | ከ 15 በላይ ሰዎች | 20 | |
| 4 | ለኤክስፖርት የሚሆን ምርት የሚያመርት ወይም ከውጭ የሚገባ ምርትን የሚተካ ምርት አምራች ከሆነ/ች | ለኤክስፖርት የሚሆን የሚያመርት ከውጭ የሚገባ ምርትን የሚተካ | 15<br>14 | 15 |
| 5 | ምርታማነቱን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሳደገ የመጣ | | | 10 |
| 6 | አዳዲስ ፈጠራ ያለው | | | 10 |
| 7 | ዘመናዊ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ የሚጠቀም | | 10 | 15 |
| | ድምር | | | 100% |

## 7. ከሞዴል ኢንተርፕራይዞች ውስጥ በሴቶችን፣ በወጣቶችን እና በአካል ጉዳተኞች የተቋቋሙ ኢንተርፕራይዞችን ሽልማት ልየታ

በየበጀት ዓመት ከተለዩት ከሞዴል ኢንተርፕራይዞች ውስጥ 30 በመቶ ሴቶች፣ 10 በመቶ የዩኒቨርሲቲ ምሩቃን፣ 4 በመቶ የአካል ጉዳተኛ እውቅና እንዲሰጣቸው የሚደረግ ሲሆን ከየክልሉ ተመልምለው ከመጡት ሴት እና የዩኒቨርሲቲና የኮሌጅ ምሩቃን ሞዴል ኢንተርፕራይዝ ውስጥ የተሻለ ውጤት ያላቸውን ከየክልሉ አንድ አንድ በመምረጥ ከሴት ሞዴል ኢንተርፕራይዝ እንዲሁም ከዩኒቨርሲቲና ኮሌጅ ምሩቃን (ወጣቶች) በመምረጥ ይሸለማሉ፡ እንዲሁም በአካል ጉዳተኛ የተቋቋሙ ኢንተርፕራይዞች ከየክልሉ አንድ አንድ በመምረጥ እንዲሸለሙ ይደረጋል፡፡

8. የWEDP ተጠቃሚ የሆኑ በሴቶች የተቋቋሙ ኢንተርፕራይዞችን ለሽልማት ልየታ

የWEDP (Women Entrepreneur Development Project) ተግባራዊ በተደረገባቸው ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ በሴቶች የተቋቋሙ ኢንተርፕራይዞችን በመለየት በፕሮጀክቱ የላቀ አፈጻጸም ያላቸውን ኢንተርፕራይዞች ለማበረታታት ያለመ ነው። የኢንተርፕራይዞች ልየታ ሂደት በአጠቃላይ በፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ከሆኑ በሴቶች ከተቋቋሙ ኢንተርፕራይዞች መካከል ከየክልሉ ከ1-3 የወጡትን በመለየት የተሻለ አፈፃፀም ያላቸውን 3 ኢንተርፕራይዞች እንዲሸለሙ ይደረጋል። ልየታውም በበፌዴራል የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ስር የሚገኘው ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚካሄድ ሲሆን የፌዴራል የከተሞች የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ መረጃውን በማጣራትና በማጽደቅ ለከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ያቀርባል።

9. በፈጠራ ሥራቸው ዕውቅና የሚሰጣቸው ኢንተርፕራይዞች የዕውቅናና ሽልማት ልየታ ሂደት

በዚህ ዕውቅና የሚሳተፉት ኢንተርፕራይዞች የፈጠራ ሥራ ካላቸው ኢንተርፕራይዞች የተሻለና የተለየ፣ ምርትና ምርታማነት የሚያሳድግና የሚጨምር፣ ከውጪ ሲገቡ የሚችሉ ምርቶችን ተክቶ ሊሰራ የሚችል እና በአምርአዊ ንብረት ጽ/ቤት ወይም ከሚመለከተው አካል የፈጠራ ሥራ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው ሊሆኑ ይገባል። ልየታው የሚካሄደው የሞዴል ኢንተርፕራይዞች መመልመያ መስፈርት መሠረት የሚፈጸም ይሆናል። የፈጠራ ሥራው የፌዴራል የከተሞች የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ አማካይነት በአካል የሚረጋገጥ ይሆናል። የአሸናፊዎችን ፕሮፋይል በዝርዝር አዘጋጅቶ ያቀርባል። በዚህም መሠረት ከየክልሉ አንድ አንድ በመምረጥ እንዲሸለሙ ይደረጋል።

10. ከስደት ተመላሾች ዜጎች የተቋቋሙ ኢንተርፕራይዞች የዕውቅናና ሽልማት ልየታ ሂደት

ከስደት ተመላሽ ዜጎች የተቋቋሙ ኢንተርፕራይዞችን ዕውቅና መስጠት ዜጎች በአገራቸው ሰርተው መለወጥ እና ማደግ እንደሚቻል ሞዴል ሆነው ያሳዩ ብሎም ለሌሎች የሥራ ዕድል በመፍጠር በአገሪቱ ልማት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ለማበርከት ያለውን ፋይዳ በመረዳት ዕውቅና መስጠት ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል።

በዚሁ መሰረት መመልመያ መስፈርት የተዘጋጀ ሲሆን የልየታ ስርአቱም ክልሎችና ከተማ አስተዳደር በመስፈርቱ መሰረት ከ1-3 የወጡትን መረጃ እና የኢንተርፕራይዞችን ፕሮፋይል እንዲልኩ ይደረጋል። የፌዴራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የተላከውን መረጃ በማጥራት ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑትን ከየክልሉ እና ከተማ አስተዳደሮች አንድ አንድ ኢንተርፕራይዞች በመምረጥ እና ውጤቱን በማጽደቅ ለከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ያቀርባል። የአሸናፊዎችን ፕሮፋይል በዝርዝር አዘጋጅቶ ያቀርባል። የስደት ተመላሽ መመልመያ መስፈርት ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፦

ሠንጠረዥ 2፡- ከስደት ተመላሽ በሆኑ ዜጎች የተቋቋሙ ኢንተርፕራይዞች መመዘኛ ነጥቦች

| ተ.ቁ | መመዘኛ ነጥቦች | የተሰጠው ክብደት% | የተሰጠው ነጥብ |
|---|---|---|---|
| 1 | ከአመለካከት አንጻር | 32% | |
| 1.1 | በሀገር ውስጥ ሰርቶ ለመለወጥ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ተደራጅቶ መስራትን በሙሉ እምነት ይዞ የሚንቀሳቀስ | 6 | |
| 1.2 | የኢንተርፕራይዙ እና የእያንዳንዱ አባላት እቅድ የተዘጋጀ መሆኑ | 3 | |
| 1.3 | ግምገማና ፍረጃ በማካሄድ የልማት ሰራዊት ግንባታ ስርአት የሚከተል መሆኑ | 5 | |
| 1.4 | የሚደረግለትን ድጋፍ ከጥገኝነትና ከኪራይ አስተሳሰብና ተግባር በጸዳ መልኩ የሚጠቀም | 6 | |
| 1.5 | ከመንግስት የሚደረግለትን ድጋፍ በመጠቀም ያመጣውን ለውጥ( ተሞክሮ) ለሌሎች የሚያስተላልፍ | 3 | |
| 1.6 | በራሱ ጥረት ማነቆዎችን የሚፈታ | 5 | |
| 1.7 | የኢንተርፕራይዙ ሴት አባላት እኩልነትን ያረጋገጠ | 4 | |
| 2 | ከክህሎት አንጻር | 27% | |
| 2.1 | የቴክኖሎጂ ፣ የሂሳብ አያያዝና የአመራር ክህሎት ያዳበረ | 5 | |
| 2.2 | የተገኘውን ክህሎት ለአባላት ለማካፈልና ለመደገፍ የሚጥር | 6 | |
| 2.3 | ምርትን ወይም አገልግሎትን በጥራት የሚያቀርብ | 6 | |
| 2.4 | ምርታማነትንና ገበያን ለማስፋት የሚጥር | 5 | |
| 2.5 | በኢንተርፕራይዙ ውስጥ የሚገኙ ባለሙያዎች የሙያ ብቃት ምዘና ያለፉ መሆናቸው | 4 | |
| 3 | ከአደረጃጀትና አሰራር አንጻር | 22% | |
| 3.1 | አባላቱ በልማት ቡድንና 1ለ5 የተደራጁ መሆናቸው | 5 | |
| 3.2 | የካይዘን ስራ አመራር የተገበረ መሆኑ | 4 | |
| 3.3 | ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ለማሳደግ የሚጥር | 3 | |
| 3.4 | የሂሳብ መዝገብ መያዝ የጀመረ | 3 | |
| 3.5 | ገበያ ለማፈላለግ የተለያዩ አሰራሮችን የሚጠቀም መሆኑ | 4 | |
| 3.6 | በአመራረት ሂደቱ የአካባቢን ብክለት ለመቀነስ /ለማስወገድ ታሳቢ ያደረገ መሆኑ | 3 | |
| 4 | ግብአቶችንና ድጋፎችን ከመጠቀም አንጻር . | 19% | |
| 4.1 | የቴክኖሎጂና የግብአት አቅርቦትን በእቅድ ውስጥ በማካተት በራሱ ጥረት ለማሟላት የሚጥር | 4 | |
| 4.2 | አባላቱ ብድር ወስደው ለታለመለት ዓላማ በማዋል ምንም አይነት ውዝፍ ሂሳብ ሳይፈጥር በየጊዜው ብድሩን የሚመልሱ መሆኑ | 4 | |
| 4.3 | ቋሚ / ጊዜያዊ የማምረቻና መሸጫ ቦታ ወስዶ ለታለመለት ዓላማ እየተጠቀመ ያለ መሆኑ | 4 | |
| 4.4 | ለኢንተርፕራይዙ የደረጃ እድገት የሚያስፈልጉ ግብአቶችን የሚጠቀም | 3 | |
| 4.5 | ኢንተርፕራዙ ከአመታዊ የሽያጭ ትርፍ ላይ 20% በማስረጃ የተደገፈ ቁጠባ ያለው፤ አባላቱም ከገቢያቸው 20 በመቶ የሚቆጥቡ መሆናቸው | 4 | |
| | ድምር | 100% | |

## ክፍል ሦስት

## ሌሎች የልማት ኃይሎች መመልመያ መስፈርቶችና የውድድር አካሄድ

### 11. ሞዴል የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ተቋማት ዕውቅና አሰጣጥ አካሄድና መስፈርት

የአንድ ማዕከል አገልግሎት ተቋሞች እውቅና መስጠት ዓላማው ተቋማቱ በሚሰጡት ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት የአፈፃፀም ደረጃቸውን በመለካት የተሻለ የአፈፃፀም ውጤት ያላቸውን በማበረታታትና ዕውቅና በመስጠት ሌሎችም ከተሞክሮቻቸው እንዲማሩ በማድረግ በመካከላቸው ጤናማ የውድድር መንፈስ እንዲፈጠር ለማድረግ ነው፡፡

ከዚህ በታች በተዘጋጀተው የተቋማቱ መመዘኛ መስፈርት መሠረት ሞዴል የአንድ ማዕከል አገልግሎት ተቋሞችን በመለየት ከየክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ከ1-3 የተሻለ ውጤት ያላቸው ተቋሞች ለፌዴራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ መረጃ እንዲልኩ ይደረጋል፡፡

የፌዴራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የተላከውን መረጃ በማጥራት ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑትን ከየክልሉ እና ከተማ አስተዳደሮች አንድ አንድ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ተቋሞችን በመምረጥ እና ውጤቱን በማጽደቅ ለከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ያቀርባል፡፡ በዚህም መሰረት ተቋማቱ መመዘኛ መስፈርት ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 3፡ ሞዴል የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ተቋማት መመዘኛ መስፈርት

| ተ.ቁ. | መመዘኛ ነጥቦች | የተሰጠው ክብደት | የተሰጠው ነጥብ |
|---|---|---|---|
| 1 | **የልማት ሰራዊት በመገንባት የተሰሩ ስራዎች** | 30% | |
| 1.1 | ከማዕከሉ ባለሙያዎች 80% የሚሆኑትን ግንባር ቀደም ማድረግ የቻለ | 6 | |
| 1.2 | አመራሩ በዘርፉ ልማት ስትራቴጂ እና የድጋፍ ማዕቀፎች እንዲሁም የልማት ሰራዊት አሰራር ጋይድላይን ላይ ስልጠና የወሰደና በዕውቀት እየመራ መሆኑ | 5 | |
| 1.3 | በማዕከሉ ያሉ ባለሙያዎች በሙሉ (100%) በልማት ቡድንና በ1ለ5 ተደራጅተው ተግባራዊ እንቅስቃሴ የጀመሩ ከሆነ | 2 | |
| 1.4 | በማዕከሉ የሥራ አከባቢ ውስጥ የሚገኙ እንቀሳቃሾች በሙሉ (100%) በልማት ቡድንና በ1ለ5 ተደራጅተው ተግባራዊ እንቅስቃሴ የጀመሩ ከሆነ | 5 | |
| 1.5 | ባለሙያው ስራውን ለመስራት በዘርፉ ስትራቴጂ እና የድጋፍ ማዕቀፎች ስልጠና የተሰጠውና በቂ ዕውቀት ያለው መሆኑ | 5 | |
| 1.6 | በሁሉም አካል የተፈጠረው አደረጃጀት ኪራይ ሰብሳቢነትን የማ[illegible] መሆኑ | 4 | |
| 1.7 | በማዕከል ደረጃ የዘርፉን የህዝብ ክንፍ ለይቶ በጋራ አቅዶ መፈፀም የጀመረ | 3 | |
| 2 | **የቴክኖሎጂ አቅርቦትና አመቺ የስራ ሁኔታ መፍጠር** | 30% | |
| 2.1 | የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያው በአዲሱ ዲዛይኑ የቢሮ | 3 | |

| ተ.ቁ. | መመዘኛ ነጥቦች | የተሰጠው ክብደት | የተሰጠው ነጥብ |
|---|---|---|---|
| | አደረጃጀት መሠረት የተገነባና አገልግሎት እየሰጠ ያለ መሆን | | |
| 2.2 | በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያው በመደብ የተፈቀደው የሰው ኃይል ሙሉ በሙሉ /100%/ የተሟላለት መሆኑ | 3 | |
| 2.3 | የማዕከሉን የቢሮ ካይዘን የተገበረ (አምስቱን ማዎች መተግበር እና የካይዘን ቦርድን መጠቀም) | 2 | |
| 2.4 | በማዕከሉ የስራ ክልል ውስጥ የሚገኙ አስር በመቶ እና ከዚያ በላይ የሆኑ ኢንተርፕራይዞች የካይዘን ስርዓትን እንዲተገብሩ ያደረገ | 3 | |
| 2.5 | ከቴክኒክና ሙያ ተቋማት ጋር በጋራ በመሆን በዕቅዱ መሰረት 90 ከመቶ ፕሮቶታይፕ እንዲዘጋጅ ያደረገ እና የተዘጋጀውን ፕሮቶታይፕ ለኢንተርፕራይዞች ሙሉ ለሙሉ ያስተላለፈ ከሆን፣ | 2 | |
| 2.6 | በማዕከሉ ሶስት እና ከዚያ በላይ ኮምፒተሮች፣ የፎቶኮፒ ማሽን እና እስካነር የተሟሉለት ከሆነ | 2.5 | |
| 2.7 | በማዕከሉ ባሉ ሰራተኞች ልክ ወንበርና ጠረጴዛ፣ በቂ የእንግዳ ማረፊያ ወንበሮች እና ሸልፎች የተሟላለት ከሆነ | 2 | |
| 2.8 | የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያው የኢንተርኔት መጠቀሚያ መስመር እና የክፍያ የመስመር ስልኮች የተዘረጉለት ከሆነ | 2.5 | |
| 2.9 | የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያው ባለሙያ ለሥራ መንቀሳቀሻ የሚገለገልበት ተሸከርካሪ (የመንንግ አበል) መሟላቱ | 2 | |
| 2.10 | የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያው ዘመናዊ እና ኮምፒዩተራይዝድ የሆነ የመረጃ አያያዝ አቀባበል ስርዓት መጠቀም የጀመረ ከሆነ | 3 | |
| 2.11 | የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ለአዲስ አበባ ከተማ እስከ አስራ አምስት ሺህ ነዋሪዎች ድረስ ብቻ ሲሆን ለሌሎች ግን በመንግስት የመጨረሻው መዋቅር ላይ አገልግሎቱን ለአካባቢው ህብረተሰብ ተደራሽ ያደረገ ከሆነ | 2.5 | |
| 2.12 | የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያው የአገልግሎት መረጃ መስጫና አቅጣጫ አመላካች ማለትም ማዕከሉ የሚገኝበትን አድራሻ፣ ስልክ፣ ፖስታ፣ ኢሜይል፣ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴቶች የሚያሳይ ቢልቦርድ፣ ደንበኞች /ተገልጋዮች ሲያሟሏቸው የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች የሚያሳይ መግለጫ፣ አቅጣጫ ጠቋሚ ታፔላ ለደንበኞች በሚታይ ቦታ የተቀመጠ እና በማዕከሉ የሚሰጡ አገልግሎቶችንና የሚሰጡበት የአገልግሎት ስታንዳርድ የተዘጋጀ ከሆነ፣ | 2.5 | |
| 3 | **አገልግሎትና የምርት ጥራት ስራዎች** | 10% | |
| 3.1. | በማዕከሉ የስራ ክልል ውስጥ የሚገኙና ለተስማሚነት ምዘና አስገዳጅ የሆኑ ምርቶችን የሚያመርቱ አምራች ኢንተርፕራይዞችን ሙሉ በሙሉ ለምርታቸው የተስማሚነት ምዘና ሰርተፍኬት (product standard certificate) እንዲያገኙ ማድረግ ያስቻለ | 1.5 | |
| 3.2 | በማዕከሉ የስራ ክልል ውስጥ ከሚገኙ አምራች ኢንተርፕራይዞች ውስጥ 25 በመቶው ለምርቶቻቸው መለያ (product brand) እንዲያሰጡ ያስደረገ | 1.5 | |
| 3.3 | በማዕከሉ አገልግሎት አሰጣጥ በተቀመጠው የቢፒአር ስታንዳርድ መሰረት እየተሰጠ መሆኑ | 1.5 | |
| 3.4 | ማዕከሉ ለሥራ ፈላጊዎችና ለአንቀሳቃሾች የሚያደረገው ድጋፍ የዘርፉን ልማት ስትራቴጂና የአሰራር መመሪያዎችና ማንዋሎችን መሠረት ያደረገ ጥራት ያለውና የተሟላ ከሆነ | 1.5 | |

| ተ.ቁ. | መመዘኛ ነጥቦች | የተሰጠው ክብደት | የተሰጠው ነጥብ |
|---|---|---|---|
| 3.5 | አጠቃላይ በማዕከሉ የሚገኙት ኢንተርፕራይዞች ጥራት ያለው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት እንዲዘረጉ ማድረግ ያስቻለ ከሆነ | 2 | |
| 3.6 | ማዕከሉ በበጀት ዓመቱ ሁለት ከውጭ የሚገባ ምርት ተክተው የሚያመርቱ ወይም ሳኪ ኢንተርፕራይዞችን ያፈራ ከሆነ | 2 | |
| 4 | የኢኮኖሚ ኢንፍራስትራክቸር ስራ | 8% | |
| 4.1 | በከተማ አስተዳደሩ ወይም በማዕከሉ ቁጥጥር ሥር የሚገኙ የማምረቻና መሸጫ ቦታዎች ሙሉ በሙሉ (100%) ለተጠቃሚዎች በአግባቡ (ለሚመለከተው አካል) መተላለፉን ያረጋገጠ፣ | 2 | |
| 4.2 | ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በከተማ አስተዳደሩ ወይም በማዕከሉ ቁጥጥር ሥር የሚገኙ የማምረቻና መሸጫ ቦታዎች ሙሉ በሙሉ (100%) መሰረተ ልማት እንዲሟላላቸው ያደረገ፣ | 1.5 | |
| 4.3 | ከከተማው አስተዳደር ጋር በመተናጀት የአከባቢውን ኢንተርፕራይዞች ፍላጎት ሊያሟሉ የሚችሉ የማምረቻና መሸጫ ቦታዎች በወቅቱ እንዲዘጋጁ ማድረግ ያስቻለ፣ | 1.5 | |
| 4.4 | የመምረቻና መሸጫ ቦታዎች ድጋፍ ተጠቃሚ የሆኑ ኢንተርፕራይዞች በከተማ አስተደደሩ ውሳኔ መሰረት መክፈል ያለባቸውን ወራሀዊ ኪራይ ሙሉ በሙሉ ያስከፈለ፣ (1.5) | 1.5 | |
| 4.5 | በማምረቻና መሸጫ ቦታ አቅርቦት ድጋፍ የዕቅድ አፈጻጸም የሴቶች ተጠቃሚነትን 50% ማረጋገጥ የቻለ፣ | 1.5 | |
| 5 | የገበያ ኢፍራስትራክቸር ሥራዎች | 10% | |
| 5.1 | በማዕከሉ ድጋፍ ከሚያገኙ ኢንተርፕራይዞች ውስጥ አስር በመቶው የእርስ በእርስ (ኢንተርፕራይ ከኢንተርፕራይ) የገበያትስስር እንዲፈጥሩ ያደረገ | 2.5 | |
| 5.2 | በማዕከሉ ድጋፍ ከሚያገኙ ኢንተርፕራይዞች ውስጥ ሀያ በመቶው ከግልና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የገበያ ትስስር እንዲፈጥሩ ያደረገ | 3 | |
| 5.3 | በማዕከሉ ድጋፍ ከሚያገኙ ኢንተርፕራይዞች ውስጥ ሀያ በመቶው በክልሉ የገበድጋፍ መሰረተ መንግስት ካፒታል ፕሮጀክቶች የገበያ ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ያስቻለ፣ | 2 | |
| 5.4 | የተፈጠረ የገበያ ትስስር በብርና በተጠቃሚ የበጀት ዓመቱን ዕቅድ 100% ማሳካት የቻለ | 2.5 | |
| 6 | የፋይናንስ ኢንፍራስተራክቸር ሥራዎች | 12% | |
| 6.1 | ቢዝነስ ፕላን በማዘጋጀት የኢንተርፕራይዞችን የብድር አቅርቦት አፈፃፀም የበጀት ዓመቱን ዕቅድ 90% ያሟላ ከሆነ | 2.5 | |
| 6.2 | በማዕከሉ ከተሰራጨውና የመመለሻ ጊዜው የደረሰ የብድር መጠን 100% ማስመለስ የቻለ | 3 | |
| 6.3 | የበጀት ዓመቱን የቁጠባ ማሰበሰብ ዕቅድ 100% ማሳካት የቻለ | 2.5 | |
| 6.4 | በማዕከሉ ሥር የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃቸውን መሰረት ያደረገ የፋይናንስ ድጋፍ ያገኙ ከሆነ | 1.5 | |
| 4.5 | የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ብድር አቅቦት ፍላጎት ያላቸውን ኢንተርፕራይዞች ለይቶ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ ከተለዩት ውስጥ 100% ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስቻለ | 2.5 | |
| | ድምር | 100 | |

## 12. የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማት የዕውቅና አሰጣጥ አካሄድና መስፈርት

የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ተቋማት ዕውቅና መስጠት ዓላማው ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በሚሰጡት የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች የአፈፃፀም ደረጃቸውን በመለካት የተሻለ የአፈፃፀም ውጤት ያላቸውን በማበረታታትና ዕውቅና በመስጠት ሌሎችም የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ከተሞክሯቸው እንዲማሩ በማድረግ በመካከላቸው ጤናማ የውድድር መንፈስ እንዲፈጠር ለማድረግ ነው፡፡

የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ልየታ መስፈርት ከዚህ በታች የቀረበ ሲሆን በመስፈርቱ መሠረት ከየክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ከ1-3 የተሻለ ውጤት ያላቸው ተቋሞች ለፌዴራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ መረጃ እንዲልኩ ይደረጋል፡፡

የፌዴራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የተላከውን መረጃ የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲን በማሳተፍ የማጥራት እና ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑትን ከየክልሉ እና ከተማ አስተዳደሮች አንድ አንድ ተቋሞችን በመምረጥ እና ውጤቱን በማጽደቅ ለከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ያቀርባል፡፡ በዚህም መሰረት የቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሚለይበት መስፈርት ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 4፡- የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማትን መመዘኛ ነጥቦች

| ተ.ቁ | መመዘኛ ነጥቦች | የተሰጠው ክብደት | የተሰጠው ነጥብ |
|---|---|---|---|
| 1 | ከአመለካከት አንጻር | 30% | |
| | የተቋሙ ባለሙያዎች ጥ/አ/ኢንተርፕራይዞችን በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመደገፍ ያላቸው የጠራ አመለካከት | 8 | |
| | የጥ/አ/ኢንተርፕራይዞችን ድጋፍ በተመለከተ እንደተቋምና እንደግለሰብ እቅድ ማዘጋጀት | 5 | |
| | የሚሰጡ ድጋፎችን አስመልክቶ ግምገማ፣ ሂስ ግለሂስና ፍረጃ በማካሄድ ባለ ሙያዎቹን የሚገነባ መሆኑ | 6 | |
| | አስፈላጊ ስልጠናዎችን በተሟላና በጥራት የሚሰጥ መሆኑ | 6 | |
| | ምርጥ ተሞክሮዎችን ቀምሮ ለማስፋት የሚተጋ | 5 | |
| 2 | ከክህሎት አንጻር | 25% | |
| | የባለሙያዎች የሙያ፣ የቴክኖሎጂ ፈጠራ /ኩረጃ/ እና የስልጠና አሰጣጥ ብቃት | 6 | |
| | ባለሙያዎቹ የብቃት ምዘና ተፈትነው ያለፉ መሆናቸው | 5 | |
| | ኢንተርፕራይዞችን ያለባቸውን ክፍተት የመለየትና የምክር አገልግሎት የመስጠት ብቃት | 5 | |
| | የኢንተርፕራይዞችን የስራ አፈጻጸም በተመለከተ የጠራ መረጃ መያዝ | 5 | |
| | ኢንተርፕራይዞች የምዘና ማዕከል እንዲሆኑ ያስቻለ | 4 | |
| 3 | ከአደረጃጀትና አሰራር አንጻር | 20% | |
| | የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በአንድ ማእከል ውስጥ እንዲገቡ የተደረገ መሆኑ | 4 | |

| ተ.ቁ | መመዘኛ ነጥቦች | የተሰጠው ክብደት | የተሰጠው ነጥብ |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | ከአንድ ማእከል ጋር በጋራ ማቀድና በቅንጅት መስራት መኖሩ | 3 | |
| | ባለሙያዎች በልማት ቡድንና በ1ለ5 የተደራጁ መሆናቸው | 4 | |
| | ለሚሰጡ ድጋፎች ሁሉ የአሰራር ማኑዋሎች ያሉ መሆናቸው | 3 | |
| | የአፈጻጸምሪፖርት ከአንድ ማእከል ሪፖርትጋር የተናበበ መሆኑ | 2 | |
| | የካይዘን አሰራር እንዲተገበር የተደረገ መሆኑ | 4 | |
| 4 | ከድጋፍና ክትትል አንጻር | 25% | |
| | የደረጃ እድገት መሰረት ያደረገ ድጋፍና ክትትል የሚደረግ መሆኑ | 4 | |
| | ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ፓኬጆችን ( የንግድ ልማት ምክርና ካይዘን አገልግሎት ፣ የሰው ሀይልና ቴክኖሎጂ ልማት ፣ የስራ አመራርና የቴክኒክ ስልጠና) እስከ ታች መዋቅር ድረስ እየወረዱ ድጋፍና ክትትል ማድረጋቸው | 6 | |
| | የተለዩ ክፍተቶች ላይ አትኩሮት በማድረግ ድጋፍና የምክር አገልግሎት መስጠት | 5 | |
| | የኢንተርፕራይዞችን የብቃት ደረጃ እየመዘኑ ሽግግር እንዲያደርጉ ማድረግ | 6 | |
| | የቴ/ሙ/ ስልጣኞች ቢዝነስ ፕላን በማዘጋጀት ቁጠባ እንዲቆጥቡና እንዲደራጁ ምቹ ሁኔታን የፈጠረ | 4 | |
| | ድምር | 100 | |

## 13. የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት የዕውቅና አሰጣጥ ልየታ ሂደት

የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት ዕውቅና መስጠት ዓላማው ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በሰጡት የፋይናንስ ድጋፍ ውጤታማ እና ተወዳዳሪ ኢንተርፕራይዞችን በመፍጠር ላበረከቱት አስተዋጽኦ ዕውቅና ለመስጠት እንዲሁም በቀጣይም ድጋፋቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ ለማድረግ ነው፡፡

በዚህ መሰረት በሁሉም ክልሎች የሚገኙ የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት ለጥቃቅንና አነስተኛ በሰጡት ድጋፍ ከየክልሉ እና ከተማ አስተዳደሮች አንድ አንድ ተቋሞችን በመምረጥ ለፌዴራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ መረጃውን በመላክ በተወካዮች አማካይነት በኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ላይ በመገኘት እውቅና እንዲሰጣቸው የሚደረግ ይሆናል፡፡

## 14. በ2009 እና 2010 በጀት ዓመት በዘርፉ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የላቀ አፈፃፀም ያስመዘገቡ የሴክተር ተቋማት እውቅና እና ሽልማት

በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በተለዩ 9 (ዘጠኝ) ፒላሮች መሠረት ባለፉት ሁለት የበጀት ዓመታት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የላቀ አፈፃፀም ላስመዘገቡ የዘርፉ ተቋማት የሚሰጥ ዕውቅና እና ሽልማት ሲሆን የዘርፉ 16ተኛው ሴክተር ጉባኤ በተካሄደበት ወቅት የማወዳደሪያ መስፈርቱ ተሻሽሎና ሥርዓቱ ይበልጥ ዳብሮ በቀጣይ ተግባራዊ እስኪሆን ድረስ ለጊዜው ዕውቅና እና ሽልማት

መስጠቱ እንዲዘገይ የተወሰነ መሆኑ ይታወሳል። ሆኖም በዚህ የ8ኛው የከተሞች ፎረም ለዘርፉ ተቋማት ዕውቅና እና ሽልማት መስጠቱ ከሚቋረጥ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በራሳቸው መስፈርት ከከተማ ልማትና ቤቶች ዘርፍ ተቋሞቻቸው መካከል የተሻለ አፈጻጸም ያስመዘገቡትን በመለየት ዕውቅና መስጠት እንደሚገባ ታምኖበታ። በመሆኑም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች አንድ ተቋም/የሥራ ሂደት/ ኤጀንሲ/ ጽ/ቤት አወዳድረው እንዲያሳውቁ በማድረግ ዕውቅና እና ሽልማት እንዲያገኙ የሚደረግ ይሆናል።

## 15. በሥነ-ጽሑፍ እና በሥዕል ውድድር ለተሳተፉ ህጻናት ዕውቅናና ሽልማት ልየታ ሂደት

በጅግጅጋ ከተማ የሚገኙ ህጻናት በከተማ ልማት አጀንዳ ዙሪያ በሥነ-ጽሑፍና በሥዕል ውድድር እንዲያደርጉ ያስፈለገበት ምክንያት ህጻናቱ በከተሞች አጀንዳ ዙሪያ ያላቸውን ግንዛቤ ከማሳደጉ በተጨማሪ ለፎረሙ ድምቀት የራሱን አስተዋጽኦ ያበረክታል። በመሆኑም በሥነ-ጽሑፍና በሥዕል ውድድር ለተሳተፉ ህጻናት እውቅናና ሽልማት ለመስጠት የከተማው የሚመለከተው አካል መመልመያ መስፈርት አዘጋጅቶ ህጻናቱን መርጦ በማቅረብ የከተሞች ራስን ማስተዋወቅ በሚካሄደባቸው ዕለታት ውድድሩን በበላይነት የሚያስተባብር ይሆናል። ከተወዳዳሪዎች መካከልም በሥነ-ጽሑፍ ከ1-3 የወጡ እንዲሁም በሥዕል ውድድር ከ1-3 የወጡ በአጠቃላይ 6 (ስድስት) ህጻናትን በመምረጥ እና ውጤቱን በማጽደቅ ለከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር በማቅረብ ሽልማት እንዲሰጣቸው ያደርጋል።

## 16. የከተማ ልማትና ቤቶች ዘርፍ የወጣቶች የፈጠራ ሥራ ዕውቅናና ሽልማት ልየታ ሂደት

በከተማ ልማትና ቤቶች ዘርፍ አጀንዳዎች ዙሪያ የፈጠራ ሥራዎችን በማበረታታት ከተሞቻችን ለኑሮ እና ለሥራ ምቹ እንዲሆኑ ከማድረግ አንጻር እንዲሁም የወጣቶችን የፈጠራ ችሎታ ከማሳደግ አኳያ አስፈላጊ ሆኖ ስለታመነበት የሥራ ፈጠራ ያላቸውን ወጣቶች በፎረሙ እውቅና እንዲያገኙ የሚደረግ ይሆናል። የፈጠራ ሥራ ያበረከቱ እና የፈጠራ ሥራው ተግባራዊ የተደረገ ወይም በቀላሉ በከተሞች ሊተገበር የሚችል ሆኖ በአምሮአዊ ንብረት ጽ/ቤት ወይም ከሚመለከተው አካል የፈጠራ ሥራ ማረጋገጫ ያገኙ ወጣቶች መካከል ውድድር በማካሄድ ዕውቅናና ሽልማት የሚሰጥ ይሆናል።

በዚሁ መሰረት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ባስቀመጠው የማወዳደሪያ ሥርዓት መሠረት የሚፈጸም ሆኖ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በመስፈርቱ መሰረት ከ1-3 የወጡትን መረጃ እና የተወዳዳሪ ወጣቶችን ፕሮፋይል እንዲልኩ ይደረጋል። የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርም የተላከውን መረጃ በማጥራት ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑትን በአካል ተገኝተው እንዲያስረዱ በማድረግ እና ወደየክልሎቹና ከተማ አስተዳደሮቹ በአካል በመገኘትና የፈጠራ ሥራውን ትክክለኛነት

ከሚመለከተው የሚ/ር መ/ቤቱ ተቋም ጋር በመሆን ያረጋግጣል። በመጨረሻም ከየክልሉ እና ከተማ አስተዳደሩ አንድ አንድ ወጣቶችን በመምረጥ እና ውጤቱን በማጽደቅ ለከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር በማቅረብ እንዲሸለሙ ይደረጋል። የአሸናፊዎችን ፕሮፋይል በዝርዝር አዘጋጅቶ ያቀርባል።

## 17. ሴቶች ዕውቅናና ሽልማት ልየታ ሂደት

በሴቶች ፓኬጅ በተጠቀሰው መሰረት ሴቶችን በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ተሳትፎ ዙሪያ ማንም ሳይደግፋቸው በራሳቸው ተነሳሽነት እና ትግል ውጤታማ የሆኑ እንዲሁም ከራሳቸው አልፈው ለአገራቸው/ለክልላቸው/ለከተማቸው አስተዋጽዖ ያበረከቱ ሴቶችን በማበረታታት ዕውቅና መስጠት የሴቶችን ተጠቃሚነትና ተሳታፊነት ከማሳደጉም በተጨማሪ ሴሎችን ለማነሳሳት ያለውን ፋይዳ በመገንዘብ በፎረሙ እውቅና እንዲያገኙ ይደረጋል።

በዚሁ መሰረት የሴቶችና ህጻናት ሚኒስቴር ባስቀመጠው የማወዳደሪያ ሥርዓት መሠረት የሚፈጸም ሆኖ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በመስፈርቱ መሰረት ከ1-3 የወጡትን መረጃ እና የተወዳዳሪ ሴቶችን ፕሮፋይል እንዲልኩ ይደረጋል። የሴቶችና ህጻናት ሚኒስቴርም የተላከውን መረጃ በማጥራት ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑትን ወደየክልሎቹና ከተማ አስተዳደሮቹ በአካል በመገኘትና የተመረጡትን ተወዳዳሪ ትክክለኛነት ከሚመለከተው የሚ/ር መ/ቤቱ ተቋም ጋር በመሆን ያረጋግጣል። በመጨረሻም ከየክልሉ እና ከተማ አስተዳደሮች አንድ አንድ ሴቶችን በመምረጥ እና ውጤቱን በማጽደቅ ለከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር በማቅረብ እንዲሸለሙ ያደርጋል። የአሸናፊዎችን ፕሮፋይል በዝርዝር አዘጋጅቶ ያቀርባል።

የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር * የከተሞች ፎረም ማስተባበሪያ *

## ክፍል አራት

## የሞዴል ኢንተርፕራይዞች የማወዳደሪያ መስፈርቶች የነጥብ አሰጣጥ፣ የምልመላ አፈጻጸምና የውጤት አገላለፅ ሂደት

**18.** የማወዳደሪያ መስፈርቶች

1) በዘርፉ ያለው የቆይታ ጊዜ

ሀ) እስከ 1 ዓመት --------------------------------------------------------------------15 ነጥብ

ለ) ከ1-2 ዓመት ----------------------------------------------------------------------13 ነጥብ

ሐ) ከ2-3 ዓመት ----------------------------------------------------------------------10 ነጥብ

መ) ከ3-4 ዓመት ----------------------------------------------------------------------8 ነጥብ

ሠ) 5 ዓመት --------------------------------------------------------------------------6 ነጥብ

ረ) ከ5 ዓመት በላይ ----------------------------------------------------------------2 ነጥብ

2) የካፒታል ዕድገት ልዩነት

ሀ) ከመነሻ ካፒታሉ ሁለት እጥፍ በላይ ያስመዘገበ ---------------------------25 ነጥብ

ለ) የመነሻ ካፒታሉን አንድ እጥፍ ያስመዘገበ ------------------------------------20 ነጥብ

ሐ) የመነሻ ካፒታሉን ከ75%-99%---------------------------------------------------16 ነጥብ

መ) የመነሻ ካፒታሉን ከ50%-74%---------------------------------------------------14 ነጥብ

ሠ) የመነሻ ካፒታሉን ከ25%-49%---------------------------------------------------12 ነጥብ

ረ) የመነሻ ካፒታሉን ከ10%-24% -------------------------------------------------10 ነጥብ

ሰ) የመነሻ ካፒታሉን ከ1%-9% ----------------------------------------------------8 ነጥብ

ሸ) የመነሻ ካፒታሉን እስከ 1% ---------------------------------------------------2 ነጥብ

3) የተለየ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም

ሀ) በኢንተርፕራይዙ በራሱ ተቀድቶ የተባዛና ሥራ ላይ የዋለ ከሆነ ------- 15 ነጥብ፣

ለ) በሀገር ውስጥ በሌሎች ኢንተርፕራይዞች የተቀዳና የተባዛ ከሆነ ------- 10 ነጥብ፣

ሐ) ከውጭ ሀገር ገብቶ ያለምንም ማሻሻያ ሥራ ላይ የዋለ ከሆነ -----------8 ነጥብ፣

4) ለሌሎች የፈጠረውን የሥራ ዕድል

ሀ) ከ20 ሰው በላይ -------------------------------------------------------------------20 ነጥብ

ለ) ከ15 - 19 ሰው---------------------------------------------------------------------15 ነጥብ

ሐ) ከ10 - 14 ሰው -------------------------------------------------------------------14 ነጥብ

መ) ከ 7 - 9 ሰው ----------------------------------------------------------------------13 ነጥብ

ሠ) ከ 4 - 6 ሰው ----------------------------------------------------------------------12 ነጥብ

ረ) ከ 2 - 3 ሰው ----------------------------------------------------------------------10 ነጥብ

ሰ) ለ1 ሰው ----------------------------------------------------------------------------5 ነጥብ

5) ምርታማነት

(1) ምርት ለማምረት/አገልግሎት ለመስጠት ከሌሎች ተመሳሳይ ኢንተርፕራይዞች የተለየ ፈጣን የአሰራር ዘዴ እና ብዛት ያለው ምርት ማምረት ...................... 10 ነጥብ

(2) በኢንተርፕራይዙ ውስጥ ያሉ አንቀሳቃሾች ከሌሎች ኢንተርፕራይዞች አንጻር በተመሳሳይ ጊዜ፣ በተመሳሳይ የማምረቻ መሣሪያና ጥሬ ዕቃ መጠን በፍጥነትና በብዛት ማምረት መቻላቸው ................................................................3 ነጥብ

(3) ከሌሎች ተመሳሳይ ኢንተርፕራይዞች ምርትን/አገልግሎትን ለመስጠት በአነስተኛ ዋጋ ጥራት ያለው ምርትና አገልገሎት የሚያቀርብ ................................ 2 ነጥብ

6) የምርት/አገልግሎት ጥራት

(1) የምርቱ/አገልግሎት ጥራቱ በተነጻጻሪ ከሌሎች የተሻለ መሆኑ በደንበኞች እና በመራጭ ኮሚቴ የተረጋገጠ .................................................................................. 15 ነጥብ

19. የምልመላ አፈጻጸምና የውጤት አገላለፅ ሂደቶች

1) በየደረጃው ለሚደረገው የምርጫ ሂደት ከቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ሥልጠና፣ ከአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋም፣ የከተሞች ሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ጽ/ቤት/ ኤጀንሲ፣ የወጣቶችና የሴቶች ፎረም ተወካዮችን ያካተተና የከተማ ሥራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ጽ/ቤት/ኤጀንሲ ተወካይ ሰብሳቢ የሆኑበት ኮሚቴ ይዋቀራል፡፡

2) መስፈርቱ እና የአፈፃፀም መመሪያው ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት በየደረጃው በሚገኙ አመራሮችና ባለሙያዎች ዘንድ ይሁንታ እንዲያገኝና ግልጽነት እንዲፈጠር ይደረጋል፤

3) ከምርጫው በፊት ሁሉም ነባርና አዲስ ሞዴል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በተዘጋጀው ቅፅ መሰረት እንዲመዘገቡና መረጃውም ከከተማ//ክፍለ ከተማ/ወረዳ የከተሞች ስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ጽ/ቤቶች ጀምሮ እየተረጋገጠና በእያንዳንዱ ቅጽ ላይ ማህተምና ኮሚቴዎች ፊርማ እያረፈበት ደረጃውን ጠብቆ ስከልሎች ይላካል፡፡

4) በየከተማው/ክፍለ ከተማው/ወረዳው የሚገኙ የከተማ ስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ጽ/ቤት ከነባር የኢንተርፕራይዞች መዝገብ በመነሳት በተገቢው የማወዳደሪያ መስፈርት ከእያንዳንዱ የሥራ ዘርፍ እና ንዑስ ዘርፍ አኳያ ነጥብ በመስጠትና ውጤት ላይ በመድረስ በከተማ ደረጃ ከ1ኛ እስከ 3ኛ የወጡትን ለምርጫ ከአቀረቧቸው እጩዎች ሙሉ ዝርዝር መረጃ ጋር ለዞን ከተሞች ስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ጽ/ቤት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

5) እያንዳንዱ የሆነ የከተሞች ስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ጽ/ቤት ጽ/ቤቶች/መምሪያዎች ከየከተሞች/ከየወረዳዎች ከየሥራ መስኩ ተመርጠው የተላኩትን ኢንተርፕራይዞች ዝርዝር መረጃ በማጣራት ከቀረቡለት ኢንተርፕራይዞች ውስጥ ከየሥራ መስኩ ማለትም ከዋና ዋና ንዑስ ዘርፎች ውስጥ በማወዳደሪያ መስፈርቱ አወዳድሮ ከየመስኩ በዞን ደረጃ ከ1ኛ እስከ 3ኛ የወጡትን ለምርጫ ከአቀረቧቸው ዕጩዎች ሙሉ ዝርዝር መረጃ ጋር ለክልሉ የከተሞች ስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ጽ/ቤት መረጃውን ይልካል፡፡

6) እያንዳንዱ የክልል የከተሞች ሥራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ወይም ቢሮ ከየዞኑ/ከተሞች ተመርጠው የተላኩለትን ኢንተርፕራይዞች በመስፈርቱ መሠረት በማወዳደር በክልል ደረጃ ከዋና ዋና ንዑሳን ዘርፎች ከ1ኛ እስከ 3ኛ ደረጃ ያገኙትን ሞዴሎች ከየሥራ መስኩ በመለየት በሚመለከተው የክልል የበላይ አካል በማጸደቅ በዕጩነት ካወዳደራቸው ኢንተርፕራይዞች ሙሉ ዝርዝር መረጃ ጋር ለፌዴራል የከተሞች ሥራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ይልካል፡፡

7) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን በተመለከተ፡-

ሀ) የወረዳ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽ/ቤት ለክ/ከተማው የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽ/ቤት፣

ለ)የክፍለ-ከተማው የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽ/ቤት ለከተማው የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ፣

ሐ) የከተማው አስተዳደር የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ከየሥራ መስኩ/ከየንዑሳን ዘርፎች ከ1ኛ-3ኛ የወጡትን በሚመለከተው የበላይ አካል በማጸደቅ ለፌዴራል የከተሞች ስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ይልካል፡፡

8) የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርና የሀረሪ ክልልን በተመለከተ፡-

ሀ) የቀበሌ የከተሞች ስራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ጽ/ቤት ለከተማው የከተሞች ስራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ፣

ለ) የከተማው/የክልሉ የከተሞች ስራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ በሚመለከተው የበላይ አካል በማጸደቅ ለፌዴራል የከተሞች ስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ይልካል፡፡

9) ፌዴራል የከተሞች ሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ከየክልሉ ተመርጠው የተላኩለትን ከየንዑስ ዘርፉ ከ1-3 የወጡትን ሞዴል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መረጃ እና ወደታዳጊ መካከለኛ የተሸጋገሩትን ኢንተርፕራይዞች መረጃ አጣርቶ ለከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር በመላክ ለከተሞች ፎረም ላይ እውቅናና ሽልማት እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

## 20. የፎረሙ ተሳታፊ ኢንተርፕራይዞች የወጪ አሸፋፈን

ከየክልሉ ተመርጠው በዕውቅናና ሽልማት ፕሮግራሙ መድረክ ላይ ከ1-3ኛ የወጡት ሞዴል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የውሎ የመጓጓዣ እና የውሎ አበል ወጭዎች ከየመጡበት ክልል ወይም ከተማ የሚሸፈን ሲሆን ወደ ታዳጊ መካከለኛ የተሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች አጠቃላይ ወጪያቸው በራሳቸው በኢንተርፕራይዞቹ የሚሸፈን ይሆናል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 21. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ሊሻሻል ይችላል።

### 22. ከመመሪያው ጋር የሚቃረን መመሪያ ወይም አሰራር

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያና ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

### 23. መመሪያው የሚጸናበት ቀን

ይህ መመሪያ ከመስከረም 07 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ጃንጥራር አባይ

የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ሚኒስትር

## 24. የመረጃ ማሰባሰቢያና ማወዳደሪያ ቅፆች

1) በ2010 በጀት ዓመት ወደ መካከለኛ የተሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች ዝርዝር መሠረታዊ መረጃ መሰብሰቢያ ቅጽ፤

ክልል__________ ዞን__________ ከተማ__________ ወረዳ/ቀበሌ__________

| ተ.ቁ | የኢንተርፕራይዙ ስም | አድራሻ | | | የተሰማራበት ሥራ | | የተቋቋመበት ዓ.ም | የካፒታል መጠን | | የአባላት ብዛት | | | | | | ለሌሎች የፈጠሩት የስራ እድል | | | | | | | | | የግብርከፋይነት መለያ ቁጥር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዞን | ከተማ | ስልክ | ዘርፍ | ንዑስ | | መነሻ | አሁን | ስራ ሲጀምር | | | አሁን | | | ቋሚ | | | ጊዚያዊ | | | ድምር | | | |
| | | | | | | | | | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

የመዝጋቢው ስም__________ ያረጋገጠው ኃላፊ ስም__________

ኃላፊነት__________ ኃላፊነት__________

ፊርማ__________ ፊርማ__________

ቀን__________ ቀን__________

2) የሞጁል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች (ከአነስተኛ አምራች ዘርፍ ውጭ) መመዝገቢያ ቅጽ፤

ክልል_______________ ዞን_______________ ከተማ_______________ ወረዳ/ቀበሌ_______________

| ተ.ቁ | የኢንተርፕራይዙ ስም | አድራሻ | | | የተሰማራበት ሥራ | | የተቋቋመበት ዓ.ም | የካፒታል መጠን | | የአባላት ብዛት | | | | | | ለሌሎች የፈጠሩት የስራ እድል | | | | | | | | | የግብርከፋይነት መለያ ቁጥር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዞን | ከተማ | ስልክ ቁጥር | ዘርፍ | ንዑስ ዘርፍ | | መነሻ | አሁን | ስራ ሲጀምር | | | አሁን | | | ቋሚ | | | ጊዜያዊ | | | ድምር | | | |
| | | | | | | | | | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

የመዘጋቢው ስም_______________

ኃላፊነት_______________

ፊርማ_______________

ቀን_______________

ያረጋገጠው ኃላፊ ስም_______________

ኃላፊነት_______________

ፊርማ_______________

ቀን_______________

3) በሴቶች የተቋቋመ/የተመሰረተ ሞዴል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች (ከአነስተኛ አምራች ዘርፍ ውጭ) መመዝገቢያ ቅጽ፣

ክልል_______________ ዞን_______________ ከተማ_______________ ወረዳ/ቀበሌ_______________

| ተ.ቁ | የኢንተርፕራይዙ ስም | አድራሻ | | | የተሰማራ በት ሥራ | | የተቋቋመበት ዓ.ም | የካፒታል መጠን | | የአባላት ብዛት | | | | ለሴሎች የፈጠሩት የስራ እድል | | | | | | | | | የግብርከፋይነት መለያ ቁጥር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዞን | ከተማ | ስልክ ቁጥር | ዘርፍ | ንዑስ ዘርፍ | | መነሻ | አሁን | ስራ ሲጀምር | | አሁን | | ቋሚ | | | ጊዜያዊ | | | ድምር | | | |
| | | | | | | | | | | ሴ | ድ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

የመዘጋቢው ስም _______________

ኃላፊነት _______________

ፊርማ _______________

ቀን _______________

ያረጋገጠው ኃላፊ ስም _______________

ኃላፊነት _______________

ፊርማ _______________

ቀን _______________

4) በአካል ጉዳተኞች የተቋቋመ/የተመሰረተ የሞዴል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች (ከአነስተኛ አምራች ዘርፍ ውጭ) መመዝገቢያ ቅጽ፣

ክልል_______________ ዞን_______________ ከተማ_______________ ወረዳ/ቀበሌ_______________

| ተ.ቁ | የኢንተርፕራይዙ ስም | አድራሻ | | | የተሰማራበት ሥራ | | የተደራጀበት ዓ.ም | የካፒታል መጠን | | የአባላት ብዛት | | | | | | ለሌሎች የፈጠሩት የስራ እድል | | | | | | | | | የግብርከፋይነት መለያ ቁጥር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዞን | ከተማ | ስልክ | ዘርፍ | ንዑስ | | መነሻ | አሁን | ስራ ሲጀምር | | | አሁን | | | ቋሚ | | | ጊዜያዊ | | | ድምር | | | |
| | | | | | | | | | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

የመዝጋቢው ስም

ኃላፊነት _______________

ፊርማ _______________

ቀን _______________

ያረጋገጠው ኃላፊ ስም

ኃላፊነት _______________

ፊርማ _______________

ቀን _______________

5) የተሸላሚ ምሩቃን መረጃ መሰብሰቢያ ቅጽ

ክልል________________ ዞን________________ ከተማ________________ ወረዳ/ቀበሌ________________

| ተ.ቁ | የኢንተርፕራይዙ ስም | አድራሻ | | | የተሰማራበት ሥራ | | የተቋቋመበት ዓ.ም | የካፒታል መጠን | | አሁን ያለው የአባላት ብዛት | | | | | | ለሌሎች የፈጠሩት የስራ እድል | | | | | | | | | የግብርከፋይነት መለያ ቁጥር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዞን | ከተማ | ስልክ ቁጥር | ዘርፍ | ንዑስ ዘርፍ | | መነሻ | አሁን | ድግሪና ከዚያ በላይ | | | ቴክኒክ | | | ቋሚ | | | ጊዜያዊ | | | ድምር | | | |
| | | | | | | | | | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

የመዝጋቢው ስም________________ ያረጋገጠው ኃላፊ ስም________________

ኃላፊነት________________ ኃላፊነት________________

ፊርማ________________ ፊርማ________________

ቀን________________ ቀን________________

6) አዳዲስ ፈጠራ ያላቸው ኢንተርፕራይዞች መረጃ መሰብሰቢያ ቅጽ

ክልል__________ ዞን__________ ከተማ__________ ወረዳ/ቀበሌ__________

| ተ.ቁ | የኢንተርፕራይዙ ስም | አድራሻ | | | የተሰማራበት ሥራ | | የተቋቋመበት ዓ.ም | የካፒታል መጠን | | የፈጠራው አይነት | የአባላት ብዛት | | | ለሌሎች የፈጠሩት የስራ እድል | | | | | | | | | የግብርከፋይነት መለያ ቁጥር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | | | | ቋሚ | | | ጊዜያዊ | | | ድምር | | | |
| | | ዞን | ከተማ | ስልክ | ዘርፍ | ንዑስ | | መነሻ | አሁን | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

የመዝጋቢው ስም__________
ኃላፊነት__________
ፊርማ__________
ቀን__________

ያረጋገጠው ኃላፊ ስም__________
ኃላፊነት__________
ፊርማ__________
ቀን__________

## 25. ማወዳደሪያ ቅጾች

1) የሞዴል ጥቃቅንና አነስተኛ(ከአምራች ዘርፍ ውጭ) ኢንተርፕራይዞች ማወዳደሪያና መምረጫ ቅጽ፤

ክልል__________ ዞን__________ ከተማ__________ ወረዳ/ቀበሌ__________

| ተ.ቁ | የኢንተርፕራይዙ ስም | በዘርፉ ሥራ የቆይታ ዘመን | በመነሻና በወቅቱ ካፒታል መካከል ያለው ልዩነት | ኢንተርፕራይዙ ያሰማራው ተጨማሪ የሰው ኃይል ብዛት | የተሰየ ቴክኖሎጂ የመጠቀም አቅም | ምርታማነት | የምርት ጥራት | ድምር | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 15% | 25% | 20% | 15% | 10% | 15% | 100% | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |

የመልማይ ኮሚቴ አባላት ስም ፊርማ ቀን

1.__________ __________

2.__________ __________ __________

3.__________ __________ __________

4.__________ __________ __________

5.__________ __________

2) በሴቶች የተቋቋመ/የተመሰረተ ሞዴል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች (ከአነስተኛ አምራች ዘርፍ ውጭ) ማወዳደሪያና መምረጫ ቅጽ፤

ክልል__________ ዞን__________ ከተማ__________ ወረዳ/ቀበሌ__________

| ተ.ቁ | የኢንተርፕራይዙ ስም | በዘርፉ ሥራ የቆይታ ዘመን | በመነሻና በወቅቱ ካፒታል መካከል ያለው ልዩነት | ኢንተርፕራይዙ ያስማራው ተጨማሪ የሰው ኃይል ብዛት | የተሰየ ቴክኖሎጂ የመጠቀም አቅም | ምርታማነት | የምርት ጥራት | ድምር | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 15% | 25% | 20% | 15% | 10% | 15% | 100% | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |

የመልማይ ኮሚቴ አባላት ስም ፊርማ ቀን

1.__________ __________
2.__________ __________ __________
3.__________ __________ __________
4.__________ __________ __________
5.__________ __________

4) በምሩቃን የተቋቋሙ ተሸላሚ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች (ከአነስተኛ አምራች ዘርፍ ውጭ) ማወዳደሪያና መምረጫ ቅጽ፤

ክልል________________ ዞን________________ ከተማ________________ ወረዳ/ቀበሌ________________

| ተ.ቁ | የኢንተርፕራይዙ ስም | በዘርፉ ሥራ የቆይታ ዘመን | የተሰማራበት የስራ ዘርፍ | ለሌሎች የፈጠረው የሥራ ዕድል | ምርታማነት | አዳዲስ ፈጠራ ያለው | ለኤክስፖርት የሚሆን ምርት የሚያመርት ወይም ከውጭ የሚገባ ምርትን የሚተካ ምርት አምራች ከሆነ/ች | ዘመናዊ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ የሚጠቀም | ድምር | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 15% | 15% | 20% | 10% | 10% | 15% | 15% | 100% | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |

የመልማይ ኮሚቴ አባላት ስም ፊርማ ቀን

1.________________ ________________
2.________________ ________________ ________________
3.________________ ________________ ________________
4.________________ ________________ ________________
5.________________ ________________

3) በአካል ጉዳተኞች ተቋቋመ/የተመሰረተ የሞዴል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች (ከአነስተኛ አምራች ዘርፍ ውጭ) ማወዳደሪያና መምረጫ ቅጽ

ክልል__________ ዞን__________ ከተማ__________ ወረዳ/ቀበሌ__________

| ተ.ቁ | የኢንተርፕራይዙ ስም | በዘርፉ ሥራ የቆይታ ዘመን | በመነሻና በወቅቱ ካፒታል መካከል ያለው ልዩነት | ኢንተርፕራይዙ ያሰማራው ተጨማሪ የሰው ኃይል ብዛት | የተለየ ቴክኖሎጂ የመጠቀም አቅም | ምርታማነት | የምርት ጥራት | ድምር | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 15% | 25% | 20% | 15% | 10% | 15% | 100% | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |

የመልማይ ኮሚቴ አባላት ስም ፊርማ ቀን

1.__________ __________
2.__________ __________ __________
3.__________ __________ __________
4.__________ __________ __________
5.__________ __________

5) አዳዲስ ፈጠራ ያላቸው ሞዴል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ማወዳደሪያና (ከአነስተኛ አምራች ዘርፍ ውጭ) መምረጫ ቅጽ፤

ክልል____________ ዞን____________ ከተማ____________ ወረዳ/ቀበሌ____________

| ተ.ቁ | የኢንተርፕራይዙ ስም | በዘርፉ ሥራ የቆይታ ዘመን | በመነሻና በወቅቱ ካፒታል መካከል ያለው ልዩነት | ኢንተርፕራይዙ ያስማራው ተጨማሪ የሰው ኃይል ብዛት | የተለየ ቴክኖሎጂ የመጠቀም አቅም | ምርታማነት | የምርት ጥራት | ድምር | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 15% | 25% | 20% | 15% | 10% | 15% | 100% | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |

| የመልማይ ኮሚቴ አባላት ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| 1.________ | ________ | ________ |
| 2.________ | ________ | ________ |
| 3.________ | ________ | ________ |
| 4.________ | ________ | ________ |
| 5.________ | ________ | ________ |